# 6. ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በምስራቅ ጎጃምዞን

[1]በምንታምር ልንገርህ፣ [2]ሀረገወይን ጥሩዬ፣ [3]ልዕልና ተዘራ [4]ጌታቸው እምሬ

[1] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች (አማርኛ) ትምህርት ክፍል፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ ኢሜይል፡- lmintamir@gmail.com.

[2]. ስነ ትምህርትና ባህሪ ተቋም፣ ሳይኮሎጂ ትምህርት ክፍል፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣

[3]. ታሪክ ትምህርት ክፍል፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

[4]. ታሪክ ትምህርት ክፍል፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

**አጽኅሮተ ፅሑፍ**

ይህ ጥናት የተካሄደው“ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በምስራቅ ጎጃምዞን” በሚል ርዕስ ነው፡ ርዕሰ ጉዳዩን ለማጥናት ዋናውአነሳሽ ምክንያት የማህበረሠቡን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ማጥናትና ወደ አካዳሚያዊ ውይይት ማምጣት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ማህበረሰቡ በባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በተናጠልም ሆነ በቡድን የተፈጠረውን ግጭት እንዴት እንደሚፈታው፣ እንደሚቆጣጠረው፣ ለአካባቢውሰላምየሚያበረክተውን አዎንታዊ አስተዋፅኦ ለማሣላትና ለሌላው ማህበረሰብ ለማስተዋወቅ ካለን ፍላጎት የተነሳ ነው፡ የጥናቱ ዋና አላማምየምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ስርዓተ ክዋኔና ማህበረ-ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ ተንትኖ ማሳየት ነው፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ቀዳማይና ካዕላይ የመረጃ ምንጮች በማጠቀም፣ በምልከታ፣ በቃለ ማጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት መረጃዎች ተሰብስበዋል። የተሰበሰቡ መረጃዎች ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ባላቸውንድፈ ሃሳቦች እየተቃኙ በዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተገልፀውና ተተርጉመውቀርበዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያማላክተውየምስራቅ ጎጃምማህበረሰብ የግጭት መንስኤዎች የተፈጥሮ ሀብት ውስንነት ነው፡ በተጠኝውማህበረሰብ ዘንድ በተደጋጋሚየሚከሰቱት የግጭት ዓይነቶች ግለሰባዊና ቡድናዊ ሲሆኑ የሚበዙት በቆላማው አካባቢ ነው፡ እነዚህ ግጭቶች የሚፈቱት ከባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች መካከል አንዱ በሆነውየሽምግልና ስርዓት ነው፡ ሽምግልና በማህበረሰቡዘንድ ከምጣኔ ሀብት፣ ከስነልቦናና ከማህበራዊ ፋይዳ አንፃር ከህገመንግስታዊው ዘዴ የበለጠ አቅም ያለው እንደሆነ በጥናቱ ተደርሶበታል። እንዲሁምየተጋጩአካላትን ወደ ቀድሞሰላማቸውለመመለስ ከህገ መንግስታዊው የተሻለ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል። በጥናቱ ግኝቶች መሰረት የይሁንታ ሀሳቦች በዘርፉ ለሚሰሩ ተቋማት እና ግለሰቦች፣ ለመደበኛውየፍትህ አካላት፣ ለፖሊሲ አርቃቂዎች፣ ህግ አውጪእና ህግ አስፈጻሚአካላት ተሰጥተዋል፡፡

**ቁልፍ ቃላት:-** ግጭት፤ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ፣ ምስራቅ ጎጃም፣ ኢትዮጵያ

**1. መግቢያ**

**1.1. የጥናቱ ዳራ**

ግጭት ምንድን ነው? መንሻውስ? ግጭት እንዴት ይፈታል? ለሚሉ ጥያቄዎች ቀጥተኛና ወጥ ምላሽ ማስጠት ቢያዳግትምበተለያዩ የግጭት ዘርፎች ላይ ጥናት የሰሩ ሙሁራንን አጣቅሶ ስለምንነቱ ማብራሪያ ማስጠት ይቻላል ብሩክ (2006)፡፡ መዝገበ ቃላዊ ብያኔውን ስናይ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም (1993፣ 510) ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ግጭትን "ጥል ወይም ጠብ" በሚል ይተረጉመዋል፡፡ የ Leslu (1973፣ 226) አማርኛ እንግሊዘኛ አውዳዊ መዝገበ ቃል ግጭትን "ትግል፣ ልዩነት፣ አለመስማማት፣ ጠብ፣ ውጊያ" በማለት ይበይነዋል፡፡ ከራሳቸው የምርምር ውጤት በመነሳት Daniel፣ Bar Tal (2006) Chandan **(1995)፣ Fisher (2000)፣** Assefa (2001)፣ Zertman (1999) እና ኤልያስ (2006) ግጭት በየትኛውም የአለማችን ክፍልና ታሪክ ውስጥ ያለና ልናስወግደው የማንችለው በሰዎች የእለት ከእለት ህይወት ውሰጥ የሚከሰት ነው፡፡

አብዛኛውን ጊዜ ግጭት የሚነሳው በተፈጥሮ ሀብቶች (Natural resources) የበላይ ሆኖ በቁጥጥር ውስጥ ለማዋል በሚደረግ ውድድር ነው፡፡ ይህ ውድድር ማህበረሰቡ በፖለቲካ፣ በሀይማኖት፣ በኢኮኖሚ በማሳሰሉት መደቦች ጎራ ለይተው እንዲጋጩ ያደርጋቸዋል፡፡

Assefa (2001)፣ Fisher (2000)፣ Schmid (2000) እና Yohannes etal (2005) የግጭት መንስኤ ከፍላጐት አለማካት፣ ከሀብት ውስንነት፣ ከዓላማ ልዩነትና ከአቅርቦት እጥረት ጋር ያያይዙታል፡፡ Schmid (2000) እያይዘውም ግጭት በሀብትና በስልጣን ከፍ ያለ ደረጃ ለመድረስ በሚደረግ ጥረት የሚከሰት አለመግባባት ነው፡፡ ሲሉ Fisher (2000)፣ Boulding (1962) እና Rugmamu (2000) ደግሞ ግጭት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ቡድኖች ባላቸው ግንኙነት መካከል በሚኖር የዓላማ ልዩነት አንዱ በሌላኛው ላይ የበላይ ለመሆን ሲሻ የሚፈጠር ተቃርኗዊ ስሜት ነው በማለት በይነውታል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ሙሁራን የግጭትን ምንነትና መንስኤ ማዕረት አድርገው የበየኑ ሲሆን Coser(1970)፣ Deutch እና Coleman (2000) ደግሞ ውጤቱን ማዕረት አድርገው ግጭት በሰው ልጆች መካከል በሚፈጠር ማህበራዊ ግንኙነት የሚከሰትና ህይወት የሚቀጥፍ ቢሆንምውጤቱ ግን የሰውን አስተሳሰብና የእድገት ደረጃ ሊያሳድግ ይችላል፡፡ ይህ የሚሆነው ግጭቱን የምንቆጣጠርበት ወይንምየምንፈታበት መንገድ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ሲኖረውነው ይላሉ፡፡ ይህን በተመለከተCoser (1970) ግጭት ዘርፈ ብዙ የሆነ አዎንታዊ ጥቅሞች እንዳለው ገልፀዋል፡፡ ከጥቅሞቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ ማንነትን ለማንበትና ራስን ሆኖ ለማኘት፣

ማንነትን በዙሪያው ካሉ ሌሎች ነገሮች ለይቶ ለመጫከት፣ ህብረት ለመፍጠር፣ ወደ ጋራ ግብ ለማምጣትና ግቡን ለማሳካት ናቸው፡፡

Lambert and Myers (1999፣ 44) የተባሉ ሙሁራን ግጭት ምን አይነት ሚና ሲኖረው ጎጂና ጠቃሚ እንደሚሆን ሲያስረዱ የሚከተለውን ሀሳብ አስፍረዋል፡፡ “Conflict is destructive when [it] prevents or stops people from working, … and [when] there are uncontrolled emotions; and [it] is constructive when [it] opens people up to new ideas, develops common goals and builds a strong relationship.”

ከእነዚህ ሙሁራን ሀሳብ ሚረዳት የሚቻለው ግጭት ጎጅ የሚሆነው ሰዎች መደበኛ ስራቸውን እንዳያከናውኑ ሲያደርግ ነው፡፡ ጠቃሚየ ሚሆነው ደግሞ አዳዲስ ሃሳቦች ሲያፈልቁ፣ በአንድ አላማ ዙሪያ ሲሰለፉና ግንኙነታቸው ሲጠናከር ነው፡፡ ይህም ግጭቶች ሲፈቱ አዎንታዊ ጎን እንዲኖራቸው ጥረት ሊደረግ እንደሚገባ ያሚላክታል፡፡

በአገራችን ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው ሁለት ዓይነት የግጭት አፈታት ዘዴዎች ይገኛሉ፡፡ እነሱም ባህላዊና ህገመንግስታዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ናቸው (Alula & Getachew፣ 2008)፡፡ ከሁለቱ ዘዴዎች ግን ረጅም እድሜ ያስቆጠረው ባህላዊው የግጭት መፍቻ ዘዴ ነው Bapu & Dagne (2013)፡፡ ምክንያቱም ህገመንግስታዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በኢትዮጵያ የተጀመረው በ1960ዎቹ ሲሆን የተቀዳውም ከአውሮፓዊያ እንደሆነ Ayalew(2012) ገልፀዋል፡፡ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ አንድ ማህበረሰብ ያለበትን ቤተሰባዊና ማህበራዊ ችግሮች እና የግጭቶቹን መንስኤ በማየት የመፍትሔ አቅጣጫዎች በቤተሰብ ወይም በማህበረሰብ መካከል የሚያስቀምጥበትና ውሳኔ የሚሰጠበት ነው Abera (2003)፡፡

ዘላቂ እርቅን ከመፍጠር አንፃር ደግሞ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ ከህገ መንግስታዊው የግጭት መፍቻ ዘዴ የተሻለ እንደሆነ Ambaye (2008) እና ብሩክ (2006) ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ የአንድን ማህበረሰብ የግጭት መፍቻ ወይም መቆጣጠሪያ መንገድ ለማጥናት የግጭት አነሳሽ ምክንያቶችንና ዓይነቶችን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል ምክንያቱም እንደ መንስኤውና ዓይነቱ የግጭት መፍቻ መንገዱ የተለያየ ስለሚሆን Best (2004)፡፡

### 1.1.1. የግጭት አነሳሽ ምክንያቶችና ዓይነቶች

Katz (1965፣ 110) የተባሉ ምሁር ግጭት በሶስት ዋና ዋና መንስኤዎች (በምጣኔ ሀብት፣ በእሴት እና በስልጣን) እንደሚከሰቱ ይገልፃሉ፡፡

**የምጣኔ ሀብት ግጭት (Economic Conflict)፡ -** የግጭት መነሻ ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ነው ስንል ቡድኖች ወይም ግለሰቦች የተፈጥሮ ሀብት ውስንነት ሲያጋጥማቸው አንዳቸው ከአንዳቸው የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን በሚያደርጉት ጥረት ወደ ግጭት እንዲገቡ ያደርጋቸዋል፡፡

**የእሴት ግጭት (Conflict of Value):-** ይህ የግጭት መነሻ ምክንያት በሰውልጆች የአኗኗር ዘይቤ፣ የርዕዮተ ዓለም ምርጫና ፍላጐት መቃረን ማለትም የኑሮ መርህና እምነት ማለያየት የሚፈጠር ነው፡፡ ይህም ማለት አንዱ ስለህይወት ያለው አመለካከትና እምነት ከሌላው ጋር አልጣጣም ሲል አልያም አንዱ የሌሎችን የአኗኗር ዘይቤ በግድ እንዲከተል ጫና ሲደርስበት ይህ ዓይነቱ ግጭት ይፈጠራል፡፡

**የስልጣን ግጭት (Conflict of Power)**፡ - ይህ የግጭት መነሻ ምክንያት አንድ ቡድን ወይም ግለሰብ በሌላኛው ቡድን ወይም ግለሰብ ላይ ተፅዕኖ ሲያሳርፍ የሚፈጠር ነው፡፡ ተፅዕኖ የደረሰባቸው ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች የተነጠቁትን የሀይል ሚዛን ወደ ራሳቸው ለማስመለስ ጥረት ማድረጋቸው ስለማይቀር የስልጣን ሽኩቻው አይቀሬ ይሆናል፡፡ ይህ ግጭት እልባት የሚያገኘው አንዱ ወገን ተሸናፊነቱን ተቀብሎ የሌላኛውን ወገን የበላይነት ሲያፀድቅ ነው፡፡ ይህ የግጭት መንስኤ በግለሰቦች፣ በቡድኖች ወይም በሀገር ደረጃ ሊፈጠር ይችላል፡ በተጨማሪም በተግባቦት ሂደት በሚፈጠር አለመጣጣም ሳቢያ የሚፈጠሩ ግጭቶች እንዳሉም Katz (1965) አያይዘው ገልጸዋል፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ሰው አንድን ነገር በራሱ አመለካከት ብቻ ወስኖ ከተረጎመው ተግባቦት ይቀንሳል እና ለግጭት ምክንያት ይሆናል፡፡

### 1.1.2. የግጭት ዓይነቶች

የግጭት ዓይነቶች የተለያዩ ቢሆኑም Chandan (1995) እና Fisher (2000፣ 48) በግጭቱ የሚሳተፉ አካላትን ቁጥር መሰረት በማድረግ ግለሰባዊ፣ ቡድናዊና ዓለም አቀፋዊ ብለው በሶስት ከፋፍለዋቸዋል፡፡

**ግለሰብዊ ግጭት (Interpersonal conflict)**፡ - ይህ የግጭት ዓይነት የሚፈጠረው ሁለት ሰዎች በፍላጎት፣ በዓላማ፣ በአቀራረብና በተግባቦት መጣጣም ሲያቅታቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የዓላማ ልዩነታቸውን አጥብበውና አቻችለው መኖር ከቻሉ በመካከላቸው ያለው ተቃርኖ ይቀንሳል፡፡

**ቡድናዊ ግጭት (Intergroup conflict)**፡ - ይህ የግጭት ዓይነት የሚፈጠረው የባህልና የዘር ተመሳሳይነት ያለው ቡድን በተቃራኒ ከተፈጠረ ሌላ ቡድን ላይ የበላይ ለመሆን ሲሻ፣ ሲያገልና ሲንቅ ነው፡፡ በአቅም ውሱንነት አልያም በተለያዩ አመለካከቶች ሳቢያ ዝቅተኛነቱን አምኖ የሚቀበል ቡድን ካለ ግን ግጭቱ ዘላቂ መፍትሔ ባይኖረውም ለጊዜው እልባት ላይ ሊደርስ ይችላል፡፡

**አለም አቀፍዊ ግጭት (International conflict)**፡ - ይህ የግጭት ዓይነት በአለም አቀፍ ደረጃ የሚታይ ሲሆን በሀገራት መካከል የሚከሰት ነው፡፡ እንደ ሁኔታው የተለያየ ቢሆንም አንድ

ሀገር በሌላኛው ሀገር ላይ የሚያውጀው ጦርነትና ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ ዋነኛ ማለጫዎቹ ናቸው፡፡

### 1.1.3. የግጭት አፈታት ዘዴዎች

ስለግጭት መነሻ ምክንያቶችና ዓይነቶች የተለያዩ ባለሙያዎች የሰጡትን ሙያዊ ትንታኔ ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን በእነዚህ ምክንያቶች የተፈጠሩ ግጭቶች ወደ ከፍተኛ ጥፋት ከማምራታቸው በፊት የተለያዩ እልባት የሚሰጥባቸው መንገዶች እንዳሉ Robbins & Seema (2006) የተባሉ ሙሁራን ገልፀዋል፡፡ Blake,Shepard and Moutom(1964)፣ Imboighe (2003:5) እና Robbins& Seema (2006) የተባሉ ሙሁራንም ዋና ዋና የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሚባሉት ድርድር፣ ሽምግልና እና ዳኝነት ናቸውሲሉ በጥናታቸውአብራርተውታል፡፡

**ድርድር /Negotiation/፡** - ድርድር በግለሰብ፣ በቡድን፣ በብሔርና በሀገር መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ከሚያገለግሉ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዘዴው የሁለቱ ተቃራኒ ወገኖችን ፍላጐት ይሻል፡፡ ማለትም ተቀራርቦ ለመነጋገርና ልዩነታቸውን በውይይት ለመፍታት መፈለግ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ሁለቱ ወገኖች ይሁነኝ ብለው ሚስጠው ወደ ድርድር ካልገቡ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሁለቱን አካላት አቀራርቦ ለድርድር ዝግጁ የሚያደርግ ሶስተኛ ወገን ያስፈልገዋል፡፡

**ሽምግልና (Mediation)፡** - ሽምግልና ከግጭት መፍቻ ዘዴዎች አንዱ ሲሆን የሁለቱ ወገኖች ይሁንታ የተቸረውአካል ጉዳዩን በሰላምለመፍታት የሚጓዝበት መንገድ ነው፡፡ በዚህ የግጭት መፍቻ ስልት ሽምጋይ ሆኖ የሚቀርበውአካል ሶስተኛ ወገን ቢሆንም የሚጨረሻውየእርቅ ውሳኔ የሚተላለፈው በሁለቱ አካላት የጋራ ስምምነት ነው፡፡ ይህ ስልት ከድርድር የሚለየው በጠበኞች መካከል ገብቶ የሚያስታርቀው ሽማግሌ ሁለቱን አግባብቶ ወደ ቀድሞ ሰላማቸው ለመመለስ የሚከሄድ መሆኑ ነው፡፡ ድርድር ግን ከአንዱ ወገን እንቢታ ሲሰማይቋረጣል፡፡

**ዳኝነት (Arbitration)፡** - ይህ የግጭት መፍቻ ዘዴ ከላይ ከቀረቡት ሁለት የግጭት መፍቻ ስልቶች የሚለየው ሶስተኛው ወገን ለግጭቱ እልባት ይሆናል የሚለውን ውሳኔ የመስጠት ህጋዊ አቅም ያለው መሆኑና አጥፍቷል በተባለው ላይ ቅጣት ይጥላል፡፡ ዳኝነት ከሌሎቹ የሚለየው የጠበኞቹን ይሁንታ ሳይፈልግ ጉዳዩን መርቶና ህግን ተከትሎ ውሳኔ የመስጠት አቅም ያለው መሆኑ ነው፡፡

በመሆኑም የምስራቅ ጎጃምዞን ማህበረሰቦች ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ከማህበረሰቡ የድርድር፣ የሽምግልና እና የዳኝነት ስርዓት አንፃር ማጥናታቸው የግጭት አፈታት ፍልስፍናን ለማወቅ ያግዛል፡፡ ከዚህ ሀሣብ በመነሣት የምስራቅ ጎጃምን ማህበረሰብ ባህላዊ

የግጭት አፈታት ዘዴ ሙቼ፣ በማን፣ እንዴት እንደሚፈቱና የተፈታውግጭት በቀጣይ ዘላቂነት እንዲኖረውየሚከወንበትን መንገድ ይህ ጥናት ትኩረት ሠጥቶ ሞርምሮታል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

በምስራቅ ጎጃምየሚገኙ ማህበረሰቦች እንደ ሌሎች የአገራችን ማህበረሰቦች ሁሉ በርካታ ቁሳዊና መንፈሳዊ እሴቶች አሏቸው፡ ከመንፈሳዊ እሴቶች መካከል ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ አንዱ ነው፡፡ ይህ መንፈሳዊ እሴት ባህላዊ የተባለበት ዋናው ምክንያት የአካባቢው ማህበረሰብ ትውፊታዊ በሆነ መልኩ በዕየለቱ የሚያጋጥሙትን ግጭቶች ለመፍታት የፈጠረውና ያዳበረውበመሆኑ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በባህላዊ ዘዴውየሚገለገለውየራሱ የሆነ መተዳደሪያ ህግና ደንብአውጥቶ ነው፡፡

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ምርምር ስናደርግ ባካሄድነው የቤተ መፅሐፍትና የድረ ገፅ ዳሰሳ Netsanet (2006) የደቡብ ወሎን፣ Melese (2008) የወላይታን፣ Daniel (2016) የሚረቆን፣ ብሩክ የኩስሜን (2006)፣ ኤልያስ የሀላባን (2006) ማህበረሰቦች ባህላዊ የግጭት አፈታት ክዋኔና የክዋኔው ባለቤት በሆኑት የአካባቢው ሽማግሌዎች ሜና ላይ የሰሩትን ጥናታዊ ፅሑፍ አግኝተናል፡፡ ነገር ግን በምስራቅ ጎጃም የሚገኘው ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠረውን ግጭት በመቆጣጠርም ሆነ የማህበረሰቡን ሰላምበማስጠበቅ በኩል የሚያበረክተው አዎንታዊ አስተዋጽኦ እና ከህገ መንግስታዊው አንፃር በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው አቅም ተገቢ የሆነ ትኩረት አግኝቶ በባለሙያዎች በበቂ ሁኔታ ተሞርምሮ ለተተኪው ትውልድ ሊተላለፍ በሚችል መልኩ ተቀርሶ በስፋት አይገኝም፡ በመሆኑም የማህበረሠቡ ግጭት መቆጣጠሪያ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ማጥናትና ወደ አካዳሚያዊ ጉዳይ ለውይይት ማምጣት የዚህ ጥናት ዋነኛው አነሳሽ ምክንያት ነው፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህን ጥናት ለማጥናት ምክንያት የሆነ ን የምስራቅ ጎጃምማህበረሰብ በባህላዊው የግጭት አፈታት ዘዴ ግጭትን እንዴት እንደሚፈታውና ለሰላምየሚያበረክተውአስተዋፅኦ ለማጥናትና ለሌሎች ማህበረሰቦች ለማስተዋወቅ ነው፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የምስራቅ ጎጃምማህበረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ስርዓተ ክዋኔና ማህበረ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ ተንትኖ ማሳየት ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡-

- በማህበረሰቡ ውስጥ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መንስኤ የሆኑ ነገሮችን መሞርሞር፤
- በማህበረሰቡ ውስጥ በተደጋጋሚየ ሚፈጠሩ ግጭቶችን ማለየት፤
- ግጭቶች በማንና እንዴት እንደሚፈቱ መግለፅ፤

- ለግጭት መፍቻ የሚያገለግሉ ቁሶችን አንድምታዊ ትርጓሜማሳየት፤
- ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ያላቸውን ፋይዳ ሚዒተሽ እና
- ባህላዊውየግጭት መፍቻ ዘዴ ከህገ መንግስታዊውአንፃር ያለውን አቅምማሳየት ናቸው

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ በዋናነት የሚያተኩረውየምስራቅ ጎጃምማህበረሰብ እርስ በዕርስ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ከሚፈታባቸው መንገዶች አንዱ የሆነ ውባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በመግለፅ እና ከህገመንግስታዊውአንፃር በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን አቅም ማሳየት ላይ ነው፡፡ እዚህ ርዕሰ ጉዳይና እዚህ ቦታ ላይ ያተኮርንበት ዋናውምክንያታችን ስለተጠኝው ማህረሰብባህልና ወግ እንዲሁምየአኗኗር ዘይቤበቂ የሆነ ግንዛቤ ስላለን ነው፡፡

# 2. የምርምር ዘዴዎች

### 2.1. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በማጠቀም ተካሂዷል፡፡ ይህን የምርምር ዘዴ ማጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት የጥናቱ ዓላማየማህበረሰቡን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ስርዓተ ክዋኔ እና ማህበረ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ ተንትኖ ማሳየት ስለሆነ ነው፡፡

### 2.2. የጥናቱ አካላይ

ኢትዮጵያ የብዙ ማህበረሰብአገር ናት፡፡ ከነዚህ መካከል አንዱየምስራቅ ጎጃምማህበረሰብ ነው፡፡ የዚህ ማህበረሰብ አባላት በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃምዞን ውስጥ በሚገኙት 18 ወረዳዎች ላይ ይኖራሉ፡፡ ስለሆነ ምለዚህ ጥናት ጠቃሚየሆኑ የመስክ ሚረጃዎች የተሰበሰቡት የማህበረሰቡ አባላት ከሚገኙባቸውና ግጭት በስፋት ይከሰትባቸዋል ተብለውከታሰቡ ስድስት ወረዳዎች ላይነው፡፡ ስለዚህ የጥናቱ ተተኳሪምእነዚህ ወረዳዎች ብቻናቸው፡፡

### 2.3. ንሞና እና ናሙና

ጥናቱ በዞኑ ከሚገኙ 18 ወረዳዎች መካከል በ6ቱ ላይ የተካሄደ ሲሆን እነዚህ ወረዳዎች ዓላማ ተኮር ዘዴን በማጠቀምከቆላ፣ ከደጋ እና ወይና ደጋ የአየር ንብረት ተመርጠዋል፡፡ ከደጋ ቢቡኝ እና ስናን፣ ከወይናደጋ ማቻከል እና ጎዛምን፣ ከቆላ ባሶሊበን እና ሸበል በረንታ ናቸው፡፡ በእነዚህ ወረዳዎች ከሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች 30 ቁልፍ ሚረጃ ሰጭሰዎች በሁለት መንገዶች ተመርጠዋል፡፡ የመጀሚሪያው መንገድ ጥናቱ ከሚካሄድባቸው ወረዳዎች ባህል እና ቱሪዝምጽህፈት ቤት ኃላፊዎች ጋር በመገናኘት ባህሉን በጥልቀት የሚያውቁ 15 ሰዎች ሲሆን ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ምልከታ ለማድረግ በየቀበሌው በተዘዋወርበት ወቅት ባህል አዋቂ 15 ሰዎችን ከአካባቢው ሰው በማጠየቅ ነው፡፡ በአጠቃላይ ቃለ ማጠይቅ ያደረግንላቸው ቁልፍ ሚረጃ ሰጪሰዎች ለማሚረጥ የተጠቀምነ ውአላማተኮር የንሞና ዘዴ

ነው፡፡ ግልጽነት በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ስድስት ቡድን ተኮር ውይይት ተካሂዷል፡፡ በእያንዳንዱ የቡድን ተኮር ውይይት ስድስት ሰዎች በአማካኝ የንግግር ዘዴ ተሳትፈዋል፡፡

### 2.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት ዓይነታዊ የምርምር ንድፍ በመጠቀም ተካሂዷል፡፡ ይህን የምርምር ዘዴ ማጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት የጥናቱ ዓላማ የማህበረሰቡን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በጥልቀት ለማጥናት ነው፡፡ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት በምልከታ፣ በቃለ ማጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት የመረጃ ማሰብሰቢያ ዘዴዎች ነው፡፡ እያንዳንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ምንነትና አስፈላጊነት ትምከዚህ በታች በሰፊው ተብራርቷል፡፡

#### ሀ) ምልከታ (Observation)

በዚህ የመረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያ ሶስት ግጭቶች ሲፈቱ በተፈጥሯዊ መቼት ምልከታ ተደርጓል፡፡ በምልከታው ወቅትም በፎቶግራፍ፣ በቪዲዮ ካሜራ እና በፅሁፍ ማስታወሻዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በዚህ የመረጃ ማሰብሰቢያ ዘዴ አጥኝዎች ተሳታፊና ዳር ቁሞ ተመልካች (Non-participant observer) ነበርን፡፡ ይህን ዘዴ ማጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት የማህበረሰቡን ባህል እንዳለ ለማግኘት አመች መሳሪያ በመሆኑ ነው፡

#### ለ) ቃለ ማጠይቅ (Interview)

ቃለ ማጠይቅ የመረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያን በማጠቀምስለ ምሳራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ባህላዊ እሳቤዎች እና ትርጓሜዎች፣ ባህላዊው የግጭት መፍቻ ዘዴ እንዴት እንደሚከወንና በክዋኔ ውወቅት የሚጠቀሙባቸው ቁሶች አንድምታ በዝግና ክፍት ቃለ ማጠይቆች አማካይነት ተሰብስበዋል፡፡ ይህም የተደረገው በምልከታ ወቅት የተሰበሰቡ መረጃዎች ይበልጥ የተሟሉ እና ገላጭ እንዲሆኑ ታስቦ ነው፡

#### ሐ) የቡድን ተኮር ውይይት (focus group discussion)

በዚህ የመረጃ ማሰብሰቢያ ወቅት ለቃለ ማጠይቅ የተመረጡ ሰዎችን በቡድን በማድረግ ግልፅ ባልሆኑ መረጃዎች ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡ ይህ የተመረጠው ከላይ በቀረቡት ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ታማኒነት እንዲኖራቸው(valid) ለማድረግ ነው፡

### 2.5. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

በመረጃ ስብሰባው ሂደት ድጋፍ ያደረጉ ረዳት መረጃ ሰብሳቢዎች ስልጠና የተሰጣቸው ሲሆን መረጃውን የሰበሰቡትምበተፈጥሯዊ መቼት በአውዱ በማ ኘት ነው፡

### 2.6. የ ሚ ጃ አቀራረብእና ትንተና

ይህ ጥናት የቀረበው ገላጭ (Descriptive) እና ተርጓሚ (Interpretative) የ ጥናት ዓይነ ቶች በማከተል ነ ው፡፡ ምክንያቱም የተሠበሠበውን ሚ ጃ መግለፅ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ ሁኖ ስለተገኘ፡፡ በዚህ አቀራረብ በማጠቀም ማህበረሰቡ በባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴው ግጭቱን በሚፈታበት ወቅት የሚያከናውኗቸው ድርጊቶች፣ የሚጠቀሙባቸው ቁሶችና ህጎች ተገልጸው ቀርበዋል፡፡ በተለያዩ የግጭት ዓይነ ቶች ላይ የተከወኑ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች እንደ አውዱ (Context) ገለፃ ተደርጎባቸዋል፡፡ እንዲሁም በተደጋጋሚየ ሚከሰቱ ግጭቶችና ባህላዊውየ ግጭት አፈታት ዘዴከዘመናዊውአንፃር በማህበረሰቡዘንድየ ተጋጩአካላትን ወደ ቀድሞሰላማቸውለመመለስ ያላቸውአቅምተብራርቶ ቀርቧል። በአጠቃላይ ማህበረ-ባህላዊ እና ሀይማኖትን ማሳረት ያደረገ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ የትና፣ መቼ፣ በማን፣ ለምን አላማ፣ እንዲሁምህግና ደንብ፣ ከእነ አውዱ እና በወቅቱ የሚጠቀሙባቸውን ቁሶች እንድምታ ጥናቱ በገለፃ አሳይቷል፡፡

### 3. የ ጥናቱ ውጤት

በዚህ ክፍል የተሰበሰቡ ሚ ጃዎች ከጥናቱ አላማዎች አኳያ ተተንትነ ውቀርበዋል፡፡

#### 3.1. የ ግጭት ምንነ ት በምስራቅ ጎ ጃምማህበረሰብ

የ ምስራቅ ጎ ጃም ማህበረሰብ ስለ ግጭት የሰጡት ብያኔ በየዕለቱ ከሚያጋጥማቸው የግጭት መንስኤ ጋር የተዛመደ ነ ው፡ ከዋነ ኛ ሚ ጃ አቀባዮች መካከል ነ ጋ በለጠ(ስናን፣ የካቲት፣ 15/2011) እና ጌታቸውአንባዬ (ቢቡኝ፣ የካቲት 11/2011) እንዳሉት፡ - ግጭት ማህበረሰቡ ተገ ቢ አይደለምየ ሚለውን ጉዳይ ሚፈፅምና የሰውን ነ ገ ር የራስ ለማድረግ በሚደረግ አለመግባባት የ ሚፈጠር ጥል ነ ው፡ በእኛ መካከል መተሳሰብ አለ ሆኖምአንዳንድ ሰዎች የሰውን ንብረት ይወስዳሉ፤ ከብቶቹንና በጎ ቹን በሰውእርሻ ያስገ ባሉ፤ የሰውሚስት ያማግጣሉ፤ ያለ ተራ የ ማስኖ ውሃ ይጠቀማሉ በዚህ ምክንያት ጠብ ይፈጠራል፡፡

በተጨማሪ ቄስ ደግፌ ወዳጄ (የ ከባቢት፣ የካቲት 27/20 11 ዓ.ም) “ግጭት የ ሚባለው በሰዎች አለመጣጣም ምክንያት ሀብት የ ሚያከስር፣ ጉልበት የ ሚያባክንና ጊዜን የ ሚጨርስ ነ ው” ሲሉ የ ግጭትን ምንነ ት ባደረግንላቸውቃለ ማጠይቅ ሚለሰውልናል፡፡

#### 3.2. የ ግጭት መንስኤዎች

በማህበረሰቡ ዘንድ የ ሚፈጠሩ ብዙ ግጭቶች መን ሻ ምክንያት በትክክል ይሄ ነ ውብሎ መናገ ር አስቸጋሪ ነ ው፡ ምክንያቱም ግጭቶች በአንድ ጊዜ በሚፈጠር ሁነ ት ብቻ የ ሚማጡሳይሆኑ የ በርካታ ችግሮች ድምር ውጤት ናቸው፡ በሌላ ሀገ ር ጥናት ያደረጉት Katz (1965፣ 110)

የተባለ ሙሁር የግጭት መከሰቻ መንስኤዎች የምጣኔ ሀብት አለመጣጣም፣ የእሴት አለመጣጣም እና የስልጣን ሽኩቻ ናቸውይላሉ፡፡

Katz (1965) እንዳለውምበጥናቱ አካላይ ማህበረሰብ በተደጋጋሚየ ሚከሰቱ ግጭቶች መነሻቸው ምጣኔ ሀብት ነው፡ የማህበረሰቡ ዋነኛ መተዳደሪያ ግብርና በመሆኑ የእርሻና የግጦሽ ቦታ ለማስፋት የሚደረግ የድንበር መግፋት፤ የማስኖ ውሃ ያለ ተራ ማጠቀምና ውርስ ዋነኛ የግጭት መንስኤዎች ናቸው፡ ከዋና ሚጃ አቀባዮች መካከል በላይ ግዛቸው(ስናን፣ የካቲት 15/2011) እንዲህ ሲሉ ገልፀውልናል፡፡ "አንደኛው ድንበር ላይ ነው ግጭት እየበዛ ያለው ሁለተኛው ደግሞ በዚህ ግጦሽ ለከብቶች ሣር ሰፈሩ ሁሉ በእርሻ ተይዟል፤ ሶስተኛው የማስኖ ውሃ ነው፣ አራተኛ የወላጆቼ ንብረት እየተባለ ሰውን የሚያነ ታርከውነገር ውርስ ነው፡"

**1. የድንበር መግፋት፡** - የእርሻ ቦታ ድንበር መግፋት በዞኑ ማህበረሰብ ተደጋግሞ ለሚፈጠሩ ግጭቶች ዋነኛ መንስኤ ነው፡ ይህም ማለት አዋሣኝ የሆነን የሰው ይዞታ ወሰኑን አልፎ ወደ ራስ ይዞታ ማስገባት ነው፡ ሜሬቱ የተገፋበት ግለሰብም ዝም ብሎ ጉዳዩን ስለማያልፈው ተያይዘው ወደ ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ አቶ ተስፋዬ አዳነ (የከባቢት፣ የካቲት 27/2011 ዓ.ም)፣ አቶ አንተነህ ተስፋ (ወንቃ፣ የካቲት21/20 11) እና አቶ ደማላሽ ፈንታው (ሸበል ማጋቢት 15/2011 ዓ.ም) በቃለ ማጠይቁ እንደገለፁልን፡፡ በጥናቱ አካላይ ወረዳዎች የእርሻ ሜሬት ድንበር መግፋት በማህበረሰቡ ዘንድ በተደጋጋሚ ለሚፈጠር ግጭት ዋነኛ መንስኤ ነው፡

2. **ውርስ**፡ - ውርስ ማለት በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ቤተሰብ (እናትና አባት ወይም አያት) ያፈራውን ንብረት ትቶት በሞት ሲለይ የሚደረግ የሀብት ክፍፍል ነው፡ በዚህ ጊዜ በቤተሠብ እና በዘመዳሞች መካከል ይህ ንብረት ለእኔ ይገባኛል ጭቅጭቅ ግጭት ይፈጠራል፡፡ በጥናቱ አካላይ ማህበረሰብ ዘንድ ለሚፈጠር ግጭት ውርስ አንዱና ዋነኛው መንስኤ እንደ ሆነ የቡድን ተኮር አምስት ተወያዮችም (ባሶ፣ የካቲት፣ 12/2011 ዓ.ም) እንዲህ ሲሉ ገልፀውልናል፡፡ ውርስ ወላጆቻቸው በህይወት እያሉ ያፈሩት ንብረት ትተውት በሞት ሲለዩ ልጆቹ ንብረቱ ለእኔ ይገባል ለእኔ ይገባል በሚል ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ የቡድን አንድ ተሳታፊዎችም (ስናን፣ ማጋቢት፣ 29/2011ዓ.ም) በማህበረሰቡ ዘንድ በውርስ ይገባኛል ወንድም ከወንድሙ ከእህቱ ጋር እስከ ማዳደል እንደሚደርስ ገልፀውልናል፡፡

**3. ፍቺ**፡ - ባለትዳሮች በተለያየ ምክንያት ፍች ሲፈጽሙ የሀብት ይገባኛል ጭቅጭቅ ይፈጠራል፡፡ በዚህ ምክንያት ባል የሚስትን አባት እና ወንድም ወይም የሚስት ወገን ባልንና የባልን ወገኖች እስከ መግደል ይደርሳሉ (የቡድን ተኮር አምስት (ባሶ፣ የካቲት 12/2011 ዓ.ም) እና የቡድን ተኮር ስድስት ተወያዮች (ሸበል፣ ሚያዚያ 18/2011 ዓ.ም)፡፡ ከዚህ ሚረዳት የሚቻለው

አብረው በነበሩበት ወቅት ያፈሩትን እና ሲጋቡ ይዘውት የተገናኙትን ሀብት በፍቺ ሰዓት በአግባቡ አለማካፈል በማህበረሰብ ዘንድ ለሚፈጠር ግጭት ዋነኛ መንስኤ መሆኑን ነው፡

**4. ያለተራ የመስኖ ውሃ ማጠቀም** - በዚህ ዞን የሚኖሩ አርሶ አደሮች በአጠገባቸው ከሚያልፍ ወንዝ ጠልፈው ውሃ በማጠጣት አትክልትና ፍራፍሬን ያመርታሉ፡፡ በተመሳሳይ ሰዓት ሁለት አርሶ አደሮች ውሃ ውየእኔ ይገባኛል ጥያቄ ያነሱና ወደ ግጭት ይገባሉ፡፡ አቶ ተስፋዬ አዳነ (የከባቢት፣ የካቲት27/2011) እና ወይዘሮ አገሬ በላይ (ቀቢ፣ የካቲት 13/2011) ይህን በተመለከተ እንዲህ ሲሉ ገልፀውታል፡፡ ውሃ ከላይ ወደታች ስለሚፈስ ከላይ ያለው ገበሬ የራሱን አትክልት ለማጠጣት ውሃውን ይገድባል፡፡ ከታች ያለው ገበሬ ደግሞ የእኔ ሳይጠጣ በሚል እሠጣ ገባ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ ሚረዳት የሚቻለው የመስኖ ውሃ ያለ ተራ ማጠቀም በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ ለሚፈጠር ግጭት አንዱ መንስኤ መሆኑን ነው፡

**5. የወል ሜሬት በአግባቡ አለማጠቀም** - የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች ለዘመናት በጋራ ከብቶቻቸውን ያሠማሩበት የነበረውን የግጦሽ ቦታ /አማጋ/ የአንድ ሠፈር ወይም ቀበሌ ነዋሪዎች ይህ ሜሬት በቀድሞ ዘመን የአባቶቻችን ይዞታ ነበር በማለት ሌሎች እንዳይጠቀሙ ሲከለክሉ የግጭት መንሰኤ ይሆናል፡፡ የቡድን አራት ተወያዮች (ማቻከል፣ የካቲት 29/2011 ዓ.ም)፡፡ ደሴ ጌታሁንና ማለሰ ሰውነት (ማቻክል፣ ሚያዚያ14/2011) ሲገልጹና ከምልከታችን እንደተረዳነው የወል ሜሬት ተስማምቶ አለማጠቀም በማህበረሰቡ መካከል ለሚፈጠር ግጭት ዋነኛ መንስኤ ነው፡ ነገር ግን እንደ ላይኞቹ ተደጋግመው የሚከሰቱ ባይሆኑም በፖለቲካና በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች መንስኤ የማህበረሰቡ አባላት በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ ወደ ግጭት ይገባሉ፡፡

### 3.3. የግጭት አይነቶች

በጥናቱ አካላይ አካባቢዎች በተደጋጋሚ የሚታዩ የግጭት ዓይነቶች የተለያዩ ቢሆኑም Chandan (1995) እና Fisher (2000) በግጭቱ የሚሳተፉ አካላትን ቁጥር መሰረት በማድረግ ግለሰባዊ፣ ቡድናዊና ዓለምአቀፋዊ ብለው በሶስት ከፍለዋቸዋል፡፡ በጥናቱ አካላይ በተደጋጋሚ የሚታዩ የግጭት ዓይነቶችን ለማከፋፈል አዳጋች ቢሆንም በዚህ ጥናታዊ ፁሁፍ ውስጥ ግን የFisher (2000፣ 48) እና የChandan (1995) የግጭት ማከፋፈያ ስልትን መሠረት በማድረግ የቡድንና የግለሰብ ግጭት በማለት በሁለት ከፍለን ተመልከተናቸዋል፡፡

**1. ግለሰባዊ ግጭት (Inter personal conflict)**፡ - ይህ የግጭት ዓይነት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚፈጠረው ሁለት ሰዎች በፍላጎት፣ በዓላማ በተግባቦት ማጣጣም ሲያቅታቸው ነው፡ የጥናቱ አካላይ ማህበረሰብ የተፈጥሮ ሀብትን ተስማምቶ ባለማጠቀም በግለሰብ ደረጃ ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ይህ ግጭት የሚከሰተውም በአብዛኛው በእርሻ ሜሬት የድንበር ግፊት፣

በማኅኖ ውሃ አላግባብ ማጠቀም፡ በፍች እና በውርስ ክፍፍል ምክንያት ነው፡ ፡ (ቡድን ሶስት፣ ቢቡኝ ፣ ግንቦት 18/2011 ዓ.ም)፡ ፡

**2. ቡድናዊ ግጭት (Inter group conflict)**፡ - ይህ የግጭት ዓይነ ት በጥናቱ አካላይ ማህበረሰቦች ዘንድ የሚፈጠረው አንዱ ቡድን በሌላ ቡድን ላይ በኢኮኖሚየበላይ ለሚሆን ሲሻ፣ ሲያገልና ሲንቅ ነው፡ ፡ የዚህ ግጭት መንስኤው በአብዛኛው የወል ግጦሽ ሜሬት በአግባቡ አለማጠቀም ነው፡ ፡ (ቡድን ስድስት፣ ሸበል፣ ሚያዚያ 18/2011 ዓ.ም)፡ ፡

### 3.4 የማህበረሰቡ የግጭት መፍቻ መንገዶች

በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ በተለያዩ ምክንያቶች የተለያዩ የግለሰብና የቡድን ግጭቶች ተስተናግደዋል፤ እየተስተናገዱም ነው፤ ወደ ፊትም ይስተናገዳሉ፡ ፡ ግጭቶቹ ዘቻን፣ ድብደባን ወይም ግድያን ያስከተሉ ቢሆኑም በባህላዊና በህገ መንግስታዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች እንደሚፈቷቸው የቡድን አራት ተወያዮች (ማቻከል፣ የካቲት 27/20 11 ዓ.ም) ገልፀውልናል፡ ፡

በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ ከባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች ማካከል ደግሞ በአብዛኛው የሚተገበረው የሽምግልና ስርዓት ነው፡ ፡ የሽምግልናን ስርዓት የሚሞር ጠብት ምክንያት ሽምግልና በማህበረሰቡ ዘንድ ከአፄዎች ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና ምነጨመፅሀፍ ቅዱስ ስለሆነ እንደ አስተሜ፣ እንደ አስታራቂ አባት እና ህግ እንደሚያወጣንጉስምይቆጠራል፡ ፡ በሚሆኑምግጭት ሲከሰት የባሰ ውድመት ሳያስከትል ይፈታል ሲሉ ቄስ ድጋፊ ወዳጄ (የከባቢት፣ የካቲት 27/20 11 ዓ.ም)፣ አባ አስተራዬ ምህረት (ባሶ፣ የካቲት፣ 12/2011 ዓ.ም) እና ሜልዓከ ገነት ማኅረት ንጋቴ (ሸበል፣ ማጋቢት 25/2011 ዓ.ም) አስረድተውናል፡ ፡ የማህበረሰቡ የሽምግልና ስርዓተ ክዋኔ ምእንደሚከተለውቀርቧል፡ ፡

### 3.5. የሽምግልና ስርዓተ ክዋኔ

የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ በተለያየ ምክንያት ይጋጫል፡ ፡ ግጭቱም የግጭት ደረጃውን (ትውቂያ፣ ትውስብ፣ ጡዘት) ጡብቆ እልባት ላይ ይደርሳል፡ ፡ ነገር ግን ግጭቱ ሲከር የተለያዩ ጉዳቶች በሰውወይምበንብረት ላይ ሊደርስ ይችላል፡ ፡ ይህ ማካረርምበባህላዊ ሽምግልና ስርዓት እልባት ላይ የሚደርሰው ቅድመ እርቅ፣ የእርቅ ጊዜ እና ድህረ እርቅ ተከትሎነ ው፡ ፡ እነ ዚህ ሂደቶችምከዚህ በታች እንደሚከተለውተተንትነ ውቀርበዋል፡ ፡

#### 3.5.1.ቅድመእርቅ

ቅድመእርቅ ስርዓተ ክዋኔ የሚባለውየከረረውግጭት እልባት ላይ ከመድረሱ በፊት ያለው ሂደት ሲሆን የማህበረሰቡቅድመእርቅ ሰርዓት እንደ ግጭቱ ውጡት የተለያየ ነ ው፡ ፡

ግጭቱ ግድያን ወይም ከባድ ድብደባን ያላስከተለ ቀለል ያለ ድብደባ፣ ዘቻ ከሆነ ሁለቱም ወገን ይስማማሉ የሚሏቸውን እና የሽምግይ ሰዕብና ያላቸውን ሽማግሌዎች ይመርጣሉ፡፡ የተመረጡ ሽማግሌዎችም ተገናኝተው ችግሩን ያጡና እንዴት፣ የትና መቼ መፍታት እንዳለባቸውተወያይተውይወስናሉ፡፡ (አቶገናነ ውጎ ጃም፣ ሸበል፣ መጋቢት 15/2011 ዓ.ም)፣ (ቡድንሁለት፣ ጎዛምን ግንቦት 16/2011 ዓ.ም)፣ (ቡድን ሶስት፣ ቢቡኝ ግንቦት፣ 18/2011 ዓ.ም) እና (ሜላዓከ ገነት መሠረት ንጋቴ፣ ሸበል፣ መጋቢት 25/2011) (ቄስ ደግፌ ወዳጄ እና ሌሎች፣ ማቻክል፣ የካቲት 27/2011 ዓ.ም)

በግጭቱ የሰው ህይወት ካለፈ ወይም ግድያ ከተፈፀመ ግን ቅድመ እርቅ እነዚህ ስርዓቶች ይፈፀማሉ፡፡ በመጀመሪያ ግድያውን የፈፀመው ሠው ይሠወራል ወይም በስህተት የሰው ህይወት በእጄ አልፏል በማለት ለፖሊስ እጁን ይሰጣል፣ የገዳይ ቤተሰቦች ይሸሻሉ፡፡ ገዳዪ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ከሆነ የንስሃ አባቱ ለሶስት የሀይማኖት አባቶችና የሽምግልና ልምድ ላላቸው ሶስት ሽማግሌዎች በሳቸው የነፍስ ልጅ እጅ የሰው ህይወት መጥፋቱን ይናገራሉ፡፡

የተመረጡሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ተሰብስበው ይመክሩና ከገዳይና ከሟች ቤተሰብ አንድ አንድ ነገረፈጅ ይመርጣሉ፡፡ ነገረ ፈጆዎችንም ያግባቡና ሂደቱን እንዲያግዟቸው ያደርጋሉ፡፡ ሽማግሌዎችና የሟች ቤተሰብ ነገረ ፈጅ የሟችን ቤተሰብ ለእርቁ እንዲስማሙ ያግባቧቸዋል፤ ከዚያ ወደ ገዳይ ነገረ ፈጅ በሜድ ቤተሰቡን አግባብቶ ወደ ሽምግልና ሥርዓቱ እንዲቀርቡ ቀጠሮ ይቀጥራሉ፡፡ በቀጠሮ ቀን በነገረ ፈጆዎቻቸውአማካይነት የታራቂ ቤተሰቦች ካልተገኙ አስታራቂዎች የሁለቱ ባለአንገራ የነፍስ አባቶች የየራሣቸውን የንስሃ ልጆች ገዝተው ወደ እርቁ ቦታ ይዘዋቸው እንዲመጡ ይደረጋል፡፡ መጀመሪያ የሟች ቤተሰብ እንዲስማማ የሚደረገውም በቂም በቀል ተነሳስተው እንዳይገድሉ በማለት ነው (ቄስ ደግፌ ወዳጄ፣ የከባቢት፣ የካቲት 27/2011 ዓ.ም) ደሴ ጌታሁን እና ማለሰ ሰውነት (ማቻክል፣ ሚያዚያ 14/2011 ዓ.ም) ቡድን ሁለት (ጎዛምን፣ ግንቦት 16/2011 ዓ.ም)፡፡

### 3.5.2. የእርቅ ጊዜ

የእርቅ ጊዜ ስርዓተ ክዋኔ የሚባለው ቅድመ እርቅ ስርዓተ ክዋኔ ከተካሄደ በኋላ ግጭቱ እልባት ላይ የሚደርስበት ጊዜ ነው፡ የእርቁ እለት አስታራቂዎችና ታራቂዎች የሚሰባሰቡት ግጭቱ ግድያ ያስከተለ ከሆነ ቤተ እምነት አጥር ግቢ ነው፡ ምክንያቱም ቤተ-እምነት ሃሰት ስለማይናገር በትክክል ችግሩ ይፈታል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡ የግጭት መነስኤው የእርሻ ሜሬት፣ የወል ሜሬት፣ የማጎ ውሃ ሆኖ ነገር ግን ግድያ ካላስከተለ እርቅ የሚፈፀመው እዛው ድንበር ቦታ እና ለምለምሰር ላይ ነው፡ ይህን የሚያደርጉት ሽማግሌዎች ችግሩን በታውላይ

ሆነው አይተው እንዲፈቱት ስለሚያስችል በሚል እና ለምለም ሳር የሚመረጥበት ምክንያት ለምለምነገር በማህበረሰቡ ዘንድ የተስፋ ተምሳሌት ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡

በምልከታችን ወቅት እንዳስተዋልነው ግድያን ባስከተለ የግጭት እርቅ ጊዜ የሚከተሉት ሄደቶች ሲከናወኑ ነበር፡፡ ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ለምለም ቦታ ላይ ተቀመጡ፡ ሁለቱም ታራቂዎች ከአስታራቂዎች በተወሰነ እርቀት በዓይን ሲታይ እኩል እርቀት በሚመስል ቦታ ላይ ተቀመጡ፡ አስታራቂዎች በመጀመሪያ ሁለቱን ወገኖች ማሳሪያቸውን ከሁለቱ ወገን ለተመረጡ ሰዎች እንዲያስረክቡ አደረጉ፡፡ መስቀል የያዙ ካህናትና ሽማግሌዎች በመስመር ቆሙ፡ ከእነርሱ ፊት ለፊት ሁለት ጠመንጃዎች በመሬት ላይ ተጋደሙ አንዱ ሽማግሌ የአንዱን ጠመንጃ አፈሙዝ ሌላው ሽማግሌ የሁለተኛውን መሣሪያ አፈሙዝ ከመሬት ጋር አጣብቀው ያዙት፡፡ ይህን የሚያደርጉበትን ምክንያትም የቡድን አምስት ተወያዮች (ባሶ፣ የካቲት12/2011ዓ.ም) በውይይታችን ወቅት እንዲህ ሲሉ ገልፀውልናል፡፡ አንድም የሟች ወገን ወደ በቀሉ የሚመለስበት አጋጣሚ አገኘሁ በማለት ጠመንጃውን ነጥቆ የገዳይን ወገን እንዳያጠቃ ነው፡ ከዚያም በእድሜ ታላቅ የሆነው ሽማግሌ መረቁና የሃይማኖት አባቶች ደግሞ በጸሎት አስጀመሩት፡፡ በመቀጠል የጠመንጃዎችን አፈሙዝ ከያዙት ሽማግሌዎች መካከል አንዱ የሟችን ወገኖችን እንዲህ የሚል ቃለ መሃላ በመጀመሪያ አስፈፀማቸው፡ *“ከባለጋራዬ ጋር አልታረቅም ብል፡ ወንጀል ብፈጽም ሰው ሲፈጽም ዝም ብዬ ብመለከት ቅዱስ ገብርኤል አይማረኝ፤ እርቁን ብተው፣ ባፍረስ ሚካኤል ዳኛ ጊወርጊስ ማያዣ ይሁንብኝ“* በማለት በመጀመሪያ የሟች ወገን እርቁን ብሽር ይህ መሣሪያ አይማረኝ እያሉ ተራበተራ ማሉ በመቀጠል ገዳይና የገዳይ ወገንም ተራ በተራ ማሉና ጠመንጃውን እየተራመዱ በመስቀል ተባርከው ቆሙ፡ ጠመንጃውን የሚራመዱበትን ምክንያትም“ባጠፋ ይህ ጠበንጃ ይግደለኝ፣ ጠመንጃው ብረት ነውና ብረትም ቀዝቃዛ ስለሆነ እኔንም እንደዚህ ያቀዝቅዘኝ (ልሙት) ማለት ሲሆን በተጨማሪም በማህበረሰብ ዘንድ መሀላ ማፍረስ ቅጣቱ ምድራዊ ህይወትን ብቻ ሳይሆን ድህረ ሞት ያለውን ሰማያዊ ህይወትም እንደሚያሳጣ ስለሚታመንበት ነው፡ ባርክልኝ ዋሴ (ባሶ፣ የካቲት፣ 12/2011 ዓ.ም) እና ቄስ በላይ ተገኔ (ባሶ፣ የካቲት12/2011 ዓ.ም) ገልፀውልናል፡፡ ”

በመቀጠልም ማሳሪያው ተነሳና ሁለቱ ታራቂዎች ጉንጭ ለጉንጭ ተሳስመው ቆሙ፡ ቄሱ ፀሎት ቡራኬ አደረጉና ታራቂዎች መስቀል ተባረኩ፤ ሽማግሌዎችም በአንድ ድምፅ “የእርቁ መጀመሪያ የጥሉ መጨረሻ ያድርግልን ብለው መረቁና ተቀመጡ፡ ከሁለቱም ወገን አንድ አንድ ሰው ተመርጠና ታራቂዎች ያመጡት ቀይ/ነጭ በግ ከሽማግሌዎች ፊት እንዲያቀርቡ ተደረገ ቀይ እና ነጭ በግ ያመጡበት ምክንያት “ነጭ የሠላም ምልክት ሲሆን ቀይ በግ ደግሞ የተስፋ ምልክት እና ለመስዋትነት ለቀረቡ ሰዎች ተምሣሌት ስለሆነ ነው፡ ቀጥሎ በሽማግሌዎች በጋችሁን ጣሉ

ሲባሉ እኩል ጣሏቸው፡ ፡ እኩል በጎች የጣሉበት ምክንያት እርቁ እንደፀና የሚገልፅ ትምዕርት ሲሆን አንዱ ቀድሞ ከጣለ ግን ቀድሞ የጣለው እንደ አሸናፊ ስለሚቆጠር በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እርቁ እንዳልፀና ይቆጠራል፡ ፡ በሚጨረሻ ስጋ ተቀላቅሎ ተጠበሰና ተጐራረሱ፤ ከጠላውም ብርጭቆውን እየተቀባበሉ ጠጡ፡ ፡ ይህም አንድነትንና ውህደትን ያሚላክታል (ቡድን አምስት፣ ባሶ የካቲት 12/2011 ዓ.ም)፡ ፡

ግድያን ያላስከተለ የወል ሜሬት ግጭት የእርቅ ጊዜ አበብኑሪት ቀበሌ (የካቲት 27/2011ዓ.ም) ተገኝተን እንደተማለከትነው በመጀመሪያ ደረጃ የሁለቱም ቀበሌ ነዋሪዎች ግጭቱ በተከሰተበት የወል ቦታ ዛፍ ስር ተሰባሰቡና ሽማግሌዎች ከሁለቱምቀበሌ ጉዳዩን የሚያስረዱ ነገረፈጅ ሦስት ሦስት ሰዎችን አስሚረጡ፡ ሽማግሌዎች ከላይ ተከራካሪዎች ከታች በግራና በቀኝ (የበ-ቅርጽ ሰርተው) ተቀማጡና ቄሱ በፀሎት ከፈቱ፡ ፡ አቶ ማለሰ ሠውነት (ቅዳምን፣ የካቲት 27/2011 ዓ.ም) የተባሉ ሽማግሌ “በሉ እንግዲህ ምህረት በጐነት ያውርድልን፣ ለሽማግሌ ጽድቁን ለባላንገራ እርቁን ይስጠን” በማለት ሚረቁ እና ይህንን የወል ሜሬት በጋራ አለማጠቀምበሁለቱምቀበሌ ኗሪዎች ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በተማለከተ ሠፊ ምክር ሠጡ ፡ ከዚያ ተከራካሪዎች የቦታውን ሁኔታ በዝርዝር አቀረቡ፤ የውጣ ግባ ሂደትም ተካሄደና የጋራ ውል በማያዝ ተፈራርመው ጨረሱ፡ ፡ በሚጨረሻም ከሁለቱ ቀበሌ የመጣውን ምግብ አብረው በሉ፡ ፡ አብረውመብላታቸውምለወደፊት ኑሯቸውበጋራ መኖርን የሚያማላክት ነው፡ ፡

ሌሎች ግድያን ያላስከተሉ የግለሰብ ግጭቶችን አፈታትን በተማለከተምአቶ አንተነህ ተስፋዬ (የከባቢት፣ የካቲት 27/2011 ዓ.ም) እንዲህ ሲሉ ገልፀውልናል፡ ፡ በዳይ ፍርድ ቤት ላለማካሰስ ሲል ሰውመደብደቡን ለሽማግሌዎች ይናገራል ሽማግሌዎች ሁለቱንም ይጠሩና በዳይ ተበዳይን ብር አውጥቶ የተመታውን ቦታ በብር ያሽለታል፤ ብሩንምይሠጠዋል፤ ይህምግጥጋጤይባላል፡ ፡ ብሩም ለበዳይ ይማለስለታል፡ ፡ ምክንያቱም ተበዳዩን ማህበረሰቡ ግጥጋጤ በልቷል ብሎ ስለሚያነውረውና ብይ በላኝ ብሎ ደግሞያለ ምክንያት ይደበድበዋል ስለሚባል ነው፡ ይህ ሁሉ ክዋኔ የሚፈፀመው አንድም ውሳኔው የሽማግሌዎች ብቻ ከሆነ አንዱ ወገን በእርቁ ሳይረካ እንዳይቀርና ሁለቱ አካላት እኩል አሸናፊ ሆነው ወደ ቀድሞው ሰላማዊ ህይወታቸውበቀላሉ እንዲማለሱ ለማድረግ ይረዳቸዋል፡ ፡

በሁሉምየግጭት ዓይነቶች የማሽማገል ስራ ሲሰራ የውጣግባና የምክረ ሀሳብ የውሳኔ ሂደቶች ተግባራዊ ይደርጋሉ፡ ፡ በተጨማሪ በድርድሩ ሂደት ማጣግጥ/ካሳ/ አብሮ ይወሰናል፡ ፡ ይህ የሚደረገው ሁለቱ ወገኖች ከልብ እንዲታረቁ ነው፡ የካሳውማጠን፣ አይነትና ፍትሐዊነት በሽማግሌዎች ዳኝነት ይወሰናል እንደ በደሉ ማጠንና አይነት ይለያያል፡ ፡ ካሳውሊማለስ ወይም ላይማለስ ይችላል፡ ፡ ይህ በተቀባዩ ይሁንታ ይወሰናል፡ ፡ ብዙ ጊዜ ግን ካሳ

እንደሚይበላ ቄስ ደግፌ ወዳጄ (የከባቢት፣ የካቲት 27/2011) እንዲህ ሲሉ ገልፀውልናል፡፡ ካሳ ከተበላ በማህበረሰቡ ዘንድ እርቁ ትክክለኛ እርቅ አይሆንም ተብሎ ይታሰባል፡፡

### 3.5.3. ድህረ እርቅ

ድህረ እርቅ የሚባለው ግጭቱ እልባት ላይ ከደረሰ በኋላ ሁለቱ ወገኖች ድጋሚ ወደ ግጭት ተመልሰው እንዳይገቡ የሚደረግ ግድም የማያዝ ሂደት ነው፡ በተጨማሪም እርቁ ቀጣይነት እንዲኖረው የሚፈፀሙ ነገሮችን ይይዛል፡፡

**እግድ /ግራንት /ግድም** የሚባለው በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የተጋጩ ወገኖች ከእርቅ በኋላ እንደገና ወደ ግጭት እንዳይገቡ የሚያደርግ ኢኮሚያዊ ማዕቀብ ወይም ጫና ነው፡ የማዕቀቡ ማጠንና አይነት በታራቂዎች ይሁንታ በሽማግሌዎች ዳኝነት ይወሰናል፡፡ እግዱ በሁለቱም ወገኖች ላይ የሚጣል ሲሆን ቃል ኪዳን ያፈረሰ አካል ተጠያቂ ይሆናል (አቶ ተጐዴ ምህረቴ ባሶ፣ የካቲት፣ ሰኔ 21/2011ዓ.ም)፡፡ በእግዱ ላይ የተፈራረሙት አንድ ቅጂ ለሽማግሌ ሌላ ለፍርድ ቤት ይሠጣል ምክንያቱም ደግመው ቢጣሉ ቀድሞ እግድ ያፈረሰው ለሌላኛው ወገን የሚይመለስ ካሳ እንዲከፍል ነው፡ በሽማግሌ አልከፍልም ካለ ደግሞ በውሉ ማሰረት ተከሶ በፍርድ ቤት ይከፍላል፡፡ ይህ የሚሆነው እርቁን ፍርድ ቤት ወደ ሽምግልና ሲልክ እንጅ ጉዳዩን ፍርድ ቤት ካልያዘው ከሳሽ ውል ይፈጸምልኝ ብሎ ውሉን አያይዞ ከከሰሰ ብቻ ፍርድ ቤት ይወስናል፡፡ አቶ እርቅይሁን ወንድምአገኝ (የደብረ ሚርቆስ ከተማ ወ/ፍ/ቤት፣ ማጋቢት11/2011 ዓ.ም)

## 3.6.ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ለማህበረሰቡ ያለው ፋይዳ

የመረጃ ትንተና ውጤቱን ማሰረት በማድረግ ባህላዊው የግጭት አፈታት ዘዴ ያለውን ፋይዳ በሶስት ዋና ዋና ዘርፍ ከፋፍለን እንደሚከተለው አብራርተነዋል፡፡

### 3.6.1.ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ

ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ለማህበረሰቡ ከኢኮኖሚ አንፃር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንደሚያስገኝ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ እነሱም -

**ሀ**.ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በማህበረሰቡ ዘንድ በተሚረጡ ሽማግሌዎች ከታረቁ የሚያወጡት ገንዘብ የለም፡ ከዚህ በተጨማሪ በእርቁ ጊዜ ለተበዳይ የተከፈለ የካሳ ክፍያ ካለ በአመቱ ለበዳይ ስለሚመለስ የገንዘብ ወጪን ይቀንሳል፡፡ አቶ ማለሠ አለበል (ቢቡኝ፣ ግንቦት፣ 5/2011 ዓ.ም)

**ለ**.ግጭቱ የሚፈታው በባዓላት ቀናት ስለሆነ ገቢያቸውን አይቀንስም፡ "የእርሻ፣ የአዝመራ ስብሰባና የውቂያ ጊዜያቸውን ስለማይሻማ የኢኮኖሚ አቅማቸውን አያዳክመውም፡ ወደ ህግ ሜድግን ፋይሉ እስቲዘጋ በመመላለስ ጉልበት ይበዘብዛል፡፡ በተጨማሪም የቤታቸውን ሠብል

ትተውለብዙ ጊዜ በቀጠሮ መብዛት ምክንያት ሲመላለሱ በወቅቱ አርሶ መዝራት እና ውጤታማ መሆን አይችሉም አቶ ይዘንጋው ጌታሁን እና ቄስ ደግፌ ወዳጀ (የከባቢ፣ የካቲት 27/2011 ዓ.ም)፡ ፡

### 3.6.2. ማህበራዊ ፋይዳ

በጥናቱ አካላይ ወረዳዎች ባህላዊ እርቅ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡ ፡ ከእነ ዚህ ጠቀሜታዎች መካከል፡ - ግጭት ውስጥ ገብተውየነበሩ ወገኖች ወደ ቀድሞው ማህበራዊ ግንኙነታቸው(እድር፣ ማህበር፣ እቁብ፣ ሰንበቴና ሸሃ) በቀላሉ ለመመለስና በሰላምአብሮ ለመኖር ያስችላቸዋል፡ ፡ በተጨማሪም በግጭት ምክንያት ተፋትተው የነበሩ ባለትዳሮች እንደገና እንዲቀጥሉ እድል ይፈጥርላቸዋል፡ ፡ አቶደሜ ጌታሁን(አበብ ኑሪት፣ የካቲት 27/2011) እና አቶ አብረውካሳ(ስናን፣ ሚያዚያ 21/2011 ዓ.ም)፡ ፡ ከዚህ ሚረዳት የሚቻለው በሽምግልና እርቅ ከተፈፀመ ሁለቱም ወገኖች ወደ ቀድሞው ማህበራዊ ህይወታቸው ተመልሰው የዕለት ተዕለት ተግባሮቻቸውን በጋራ ማከናወን እንደሚችሉ ነው፡ ፡

### 3.6.3. ስነ -ልቦናዊ ፋይዳ

ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ስነ -ልቦናዊ ፋይዳ አለው፡ ከነ ዚህም መካከል፡ - አንደኛው እርቅ ከተፈፀመ በኋላ የተጋጩአካላት ምንም ስጋት እና ፍርሃት ሣይኖርባቸውየእየለት ተግባሮቻቸውን ያከናውናሉ፡ ፡ የተጣሉ ሠዎች ከታረቁ በኋላ ሳይፈሩ እንደልባቸው ወጥተው ይገባሉ፤ ሌሊትም ተረጋግተው እንቅልፋቸውን ይተኛሉ፤ ቂማቸውም ይወገዳል፣ ሠላም በውስጣቸው ይኖራል፡ ፡ ምክንያቱም ሽምግልና በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ እምነት የሚጣልበት በመሆኑ ነው ሲሉ አቶ ማለሠ ሠውነት (የከባቢት፣ 27/06/2011 ዓ.ም) እና ቄስ ደግፌ ወዳጀ (የከባቢት፣ 27/06/2011 ዓ.ም) ገልፀውልናል፡ ፡ ሁለተኛው ደግሞ በሽምግልና የሚታረቁ ሰዎች እኩል የሆነ የአሸናፊነት ስሜት ይሰማቸውና እኩል ይረካሉ፡ ፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ እርቅይሁን ወንድምአገኘም (ደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሰኔ 11/2011 ዓ.ም) እንዲህ ሲሉ ገልፀውልናል፡ ፡ "ባህላዊውእርቅ በማህረሰቡ ዘንድ ሚዛናዊ እና ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ የማስጠት አቅምአለውተብሎስሚታመን ሁለቱምወገኖች እኩል ይረኩና ሁለቱምአሸናፊ ይሆናሉ፡ ፡ "

### 3.7. ባህላዊውየ ግጭት አፈታት ዘዴ ከህገ -መንግስታዊውአንፃር ያለውአቅም

በጥናቱ ተተኳሪ አካባቢዎች ላይ ሽምግልና ከፍርድ ቤት የግጭት አፈታት ስርዓት ግጭትን በተሻለ ሚልኩ የመፍታት አቅም አለው፡ ምክንያቱም ሽማግሌዎች ግጭቱ ከምን እንደሚ ሣ ሚነጥሩን በጥልቀት ስለሚያውቁት ያለ አድሎ የተጋጩትን በማውያየት ትክክለኛ ውሣኔ ያሳርፋሉ፡ ፡ ህገመንግስታዊውየእርቅ ስርዓት ግን የግጭቱን መንስኤ ለማግኘት ምክሮችን

ይጠቀሟል፡፡ ነገር ግን ምስክሮች በጥቅማ ጥቅም ተደልለው ትክክለኛውን ሚ ጃ ላይሠጡ ይችላሉ፡፡ "ዳኛ ሰምቶ እንጂ አይቶ አይፈርድም" እንዲሉ ጉዳቱ ለሌላውሁኖ ሳለ የሚረደው ለአንደበተ ርዕቱ ስለሚሆን የተዛባ ውሳኔ ይወሰንና የተፈረደበት ወገን አስፈረድህብኝ ብሎ ሌላ ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ አቶ ተጌዴ ምህረቴና አቶ ባርክልኝ ዋሴ(ባሶ፣ የካቲት፣ 12/2011 ዓ.ም) እና ቄስ ደግፌ ወዳጀ (የከባቢት፣ የካቲት 27/2011ዓ.ም)

ይህምበፍርድ ቤት ከተወሠነ ሌላ ግጭት ይፈጥራል በሽምግልና እርቅ ከተደረገ ግን እንደገና ወደ ጥል አይገቡም፡ ምክንያቱም ባህላዊ የግጭት አፈታት ከሃይማኖት ጋር ከፍተኛ የሆነ ቁርኝት ስላለው ተቀባይነት እና እምነትን ያሳጣል፡፡ ይህን ሀሳብ አያይዘውም የቡድን ስድስት ተወያዮች (ሽበል፣ ሚያዚያ 18/2011 ዓ.ም) እንዲህ ሲሉ ገልፀውታል፡፡ የተጋጩሠዎች ምንም ቢሆን የሽማግሌ ውሣኔ ይቀበላሉ፣ የተጣሉትምበእግዚአብሔር ቃልና በማስቀሉ ምለው ስለሚታረቁ አስተማማኝ ነው፡

ከህገ መንግስታዊው ይልቅ ሽምግልና ከፍተኛ አቅም አለው፡ ምክንያቱም ገንዘብንና ጊዜን ይቆጥባል፡፡ ዘመናዊ ግን ገንዘብና ጉልበት ያባክናል፤ የተፈረደለት ወገን ይረካና የተፈረደበትን ወገን ደግሞወደ ሌላ በቀል እንዲሄድ ያደርጋል እርቁምዘለቄታ አይኖረውም፡ (አቶ እርቅይሁን ወንድሜ ህ፣ ደብረ ማርቆስ ሰኔ 11/2011 ዓ.ም)

በአጠቃላይ ከዚህ ሚዳት የሚቻለው ከታማኒነት፣ ከእርካታ፣ ዘላቂ መፍትሔ ከማስጠት፣ ከገንዘብና ከጊዜ አንፃር ባህላዊው የግጭት አፈታት ዘዴ ከዘመናዊው የተሻለ በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ አቅምአለው፡

**4. ማጠቃለያ**

ይህ ጥናት ስድስት ዋና ዋና ግኝቶችን አመላክቷል፡፡ የመጀመሪያው የጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው በምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ለሚፈጠር ግጭት ዋና መንስኤው የተፈጥሮ ሀብት ውስንነት ነው፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Katz (1965) ግጭት በሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ማለትምበምጣኔ ሀብት፣ በእሴት እና በስልጣን ምክንያት እንደሚከሰት ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁምአሰፋ (2001) አብዛኛውን ጊዜ ግጭት የሚ ሳውተፈጥሯዊ ሀብቶችን ለመቆጣጠርና የበላይ ለመሆን በሚደረግ ውድድር ነው፡ ይህ ውድድር የተለያየ ጎራ ለይተውእንዲጋጩያደርጋቸዋል ሲሉ፡፡ በዚህ ጥናት አካላይ ወረዳዎች ግን ለሚከሰት ግጭት ዋና መንስኤውኢኮኖሚነ ውማለት እንችላለን፡፡ Assefa (2001)፣ Schmid (2000)፣ Fisher (2000) እና Yohannes etal (2005) ግጭትን ከፍላጐት አለማካት፣ ከሀብት ውሱንነት፣ ከዓላማ ልዩነትና ከአቅርቦት እጥረት ጋር ያያይዙታል፡፡

ሁለተኛው ውጤት የሚያሣየው በዞኑ ማህበረሰብ ዘንድ በተደጋጋሚ የሚከሰተው የግጭት ዓይነት የግለሰብ እና የቡድን ግጭት ነው፡፡ በተመሳሳይ Fisher (2000)፣ Chandan (1995) ግጭት ውስጥ በሚሳተፉት አካላት ቁጥር በመወሰን የግጭት ዓይነቶችን ግለሰባዊ፣ ቡድናዊና ዓለምአቀፋዊ ናቸውብለዋል፡፡

ሶስተኛው ውጤት ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ በቡድንም ሆነ በግለሰብ ደረጃ የሚፈጠሩ ግጭቶች የሚፈቱት በህገ መንግስታዊውና ከባህላዊው ዘዴ አንዱ በሆነው ሽምግልና ነው፡፡ በጥናቱ አካላይ ወረዳዎች በአብዛኛው የሚተገበረው ባህላዊ እርቅም ሽምግልና ነው፡፡ ግጭቱን በሰላማዊ መንገድ የሚፈታበትና የቀድሞው ማህበራዊ ግንኙነት የሚቀጥልበት ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ጥናት ያካሄዱት Imboighe (2003)፣ Robbins እና ሌሎች (1964)) ዋና ዋና የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሚባሉት ድርድር፣ ሽምግልና እና ዳኝነት ናቸው፡፡ Alula እና Getachew (2008) በአገራችን በዋናነት ህብረተሰቡ የሚጠቀምባቸውዘዴዎች ባህላዊ እና ህገ መንግስታዊ ናቸው፡፡ ነገር ግን ሁለቱም የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በአሁኑ ሰዓት በአገራችን ተግባራዊ ይደረጉ እንጂ ረጅም እድሜ ያስቆጠረውና የማህበረሰቡ ፍላጎት በተጠበቀ መልኩ ስሜቱን ሳይጎዳ ሲያገለግል የቆየውባህላዊውየግጭት መፍቻዘዴነው Dagne and Bapu (2013)፡፡

አራተኛውየጥናት ውጤት የሚያሳየውበግጭት አፈታት ሰርዓት ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን ቁሶች በግ የማነዋትነት ተምሳሌት ሲሆን ቀዩ በግ የምድራዊ ህይወት ነጩበግ የሰማያዊ ህይወት መልካም ምኞት መግለጫሲሆን ጡበመንጃ ደግሞየሞት ተምሳሌት ነው፡

አምስተኛው የጥናት ውጤት ባህላዊው የግጭት አፈታት ዘዴ ማህበረሰቡ በግንኙነቱ ወቅት ግጭትን ፈትቶ፣ የቀድሞ ግንኙነቱን ለማጠናከርና ማህበራዊ ሰላሙን ለማስጠበቅ፣ ጊዜን፣ ጉልበትንና ምጣኔ ሀብትን በመቆጠብ፤ ስሜቱን ሳይጎዳ ችግርን ከመፍታት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በተመሳሳይ Ambaye (2008)፤ Dagne and Bapu (2013) እና ብሩክ (2006) ጉዳዩ በእርቅ ስለሚያለቅ ጊዜ እና ወጪን ከመቀነሳቸውየበለጠ ወደ ቀድሞሰላማዊ ግንኙነት ለመመለስና የማህበረሰቡን ስነልቦናዊ ደህንነት በማጠበቅ ጠቀሜታውከፍ ያለ ነው፡

ስድስተኛውውጤት የሚያሣየውሽምግልና ከዘመናዊ አንፃር በማህበረሰቡ ዘንድ የተፈጠሩ ግጭቶችን በአዎንታዊ ጎን ስለሚፈታ ና ዘላቂ እርቅን ስለሚፈጥር የተሻለ አቅምአለው፡ በተመሳሳይም Ambaye (2008) እና ብሩክ (2006) ባህላዊው የግጭት መፍቻ ዘዴ ከህገመንግስታዊውዘዴ የተሻለ አቅምእንዳለውእንዲህ ሲሉ ገልፀውታል፡፡ ጊዜና ወጪን በመቀነስ ዘላቂ መፍትሔማስጠት በመቻሉ ነው፡ ሽምግልናን ከዘመናዊውየተሻለ ያደረገው የተጋጩአካላት ለሽምጋዩ የሚሰጡት ክብርና እውቅና ነውሲሉ Abera(2003) ገልፀውታል፡፡ ብሩክ (2004) እና ያሬድ (2004) ሽምግልናን ከህገመንግስታዊውየላቀ ያደረገውግጭት ውስጥ

የገቡት አካላት በውሳኔው ተሳታፊ ሲሆኑ ህገመንግስታዊው ግን ህግን ብቻ ተከትሎ ውሳኔ ሥለሚሰጥ ነው፡፡

## 5. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋነኛውአነሳሽ ምክንያት የማህበረሠቡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴን ማጥናትና ወደ አካዳሚያዊ ጉዳይ ለውይይት ማምጣት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የምስራቅ ጎጃምማህበረሰብ በባህላዊው ዘዴ በአብዘኛው የሚገበረው ባህላዊ እርቅም ነው፡፡ የተፈጠረውን ግጭት እንዴት እንደሚፈታው፣ እንደሚቆጣጠረውና ለአካባቢው ሰላም እንዴት እንደሚያለገልበት ለማሳለት እና ለሌሎች ማህበረሰብ ለማስተዋወቅ ካለን ፍላጎት አንፃር ነው፡የጥናቱ ዋና አላማም ማህበረሰቡ የሽምግልና ስርዓተ ክዋኔና ፋይዳውን ተንትኖ ማሳየት ነው፡ይህን ዓላማከግብ ለማድረስ ሚጃዎች ተሰብስበውበዓይነታዊ ሙትንተኛ ዘዴዎች ተገልፀውስድስት ውጤቶችን አማላክቷል፡፡ አንደኛው በማህበረሰቡ ለሚፈጠር ግጭት ዋና መንስኤው የተፈጥሮ ሀብት ውስንነት፤ ሁለተኛው በተደጋጋሚ የሚከሰተው የግጭት ዓይነት የግለሰብና የቡድን ግጭት መሆኑን፤ ሶስተኛውግጭቶች የሚፈቱት ህገመንግስታዊውና ከባህላዊውዘዴዎች ማካከል አንዱ በሆነ ውሽምግልና ነው፤ አራተኛውበባህላዊውየግጭት አፈታት ወቅት የሚጠቀማት ቁስ የተፈታው ግጭት ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ በኩል ከፍተኛ ሚና መኖሩን፤ አምስተኛው ባህላዊው ዘዴ ማህበረሰቡ ግጭቶችን ፈትቶ፣ ማህበራዊ ሰላሙን ለማስጠበቅ፣ ጊዜን፣ ጉልበትንና ምጣኔ ሀብትን ከመቆጠብ፣ ስሜትን ሳይጎዳ ችግርን መፍታትና ስድስተኛውባህላዊ ከዘመናዊ አንጻር በማህበረሰቡ ዘንድ የተፈጠሩ ግጭቶችን በአዎንታዊ ጎን ከመፍታትና ከታማኒነት፣ ከእርካታ፣ ዘላቂ መፍትሔ ከማስጠት፣ ገንዘብና ጊዜን ከመቆጠብ አንፃር ባህላዊውየግጭት አፈታት ዘዴከዘመናዊውየተሻለ አቅምያለውመሆኑን ነው፡

## 6. ይሁንታ

ከጥናቱ ውጤትና ሂደት በመነሳት የተወሰኑ የይሁንታ ሃሳቦችን ማቅረብ ችለናል።

- ✓በአገራችንንምይሁን የምስራቅ ጎጃምን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴያገባኛል የሚሉ ተቋማት እና ግለሰቦች ልምዱን ወደ ተለያዩ ማህበረሰቦች ቀምሮ ማስፋፋት ቢችሉ፤
- ✓በዘርፉ የሚሰሩ ተቋማት እና ግለሰቦች ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴን ውጤታማ ለማድረግ ለሀገር ሽማግሌዎች ስልጠና በማስጠት ባህሉን ማዳበር ቢቻል፤
- ✓መደበኛው ፍርድ ቤት ደግሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴን ጠቀሜታ ለማህበረሰቡ በማሳ በማስረዳት ወደ ተቋማቸውከመምጣታቸውበፊት በሽማግሌዎች ግጭት እንዲፈቱ የግንዛቤ ስራ ቢሰሩና የእርቁን ተፈጻሚ ት ቢከታተሉ፡፡
- ✓ፖሊሲ አርቃቂ፣ ህግ አውጭእና ህግ አስፈጻሚአካላት ጉዳይን ከፍተኛ ትኩረት ቢሰጡት፡፡

## ዋቢ መፅሐፍት


Abera Jembere. (2003). Legal history of Ethiopia. Hamburg and London: Lit Verlag.

Alula Pankhurst & Getachew Assefa. (2008). Grass Roots justice in Ethiopia. Addis Ababa: French Center of Ethiopian Studies.

Alemayehu, F.(2010). The role of traditional conflict resolution mechanisms across borders: The case of Borana, Gabra and Garri communities across Ethio-Kenya Border. USA.

Ambaye Ogato. (2008). *Traditional conflict resolution mechanisms: The case of Sidama. In Hannan, T. & Tarekegn, A. (eds), making peace in Ethiopia: Five cases of traditional mechanisms for conflict resolution*. (pp. 101-120): Addis Ababa, peace and Development committee.

Assefa Abebe. (2001). Conflict in pastoralist community pastoralists in south omo." prteceding of the workshop held in Jinka (south omo). Epa RDA pp31_41

Boulding. K.(1962). Conflict and defense; A general theory, New York, Harper Raw publishers..

Best, S.G. (2004). *The methods of conflict resolution and transformation.* In Best, S.G. (ed.),*Introduction to Peace and conflict studies in West Africa* **(**pp**.**93**-**115**)**. Ibadan: spectrum Books ltd.

Blake, R.R., Shepard, H.A., & Mouton, J. S.(1964). Managing intergroup conflict in industry.Houston, Texas: Gulf.

Chandan,J.S.(1995). *Management: Theory and practice*. New Delhi:VBIKS publishing House Pvt.Ltd.

Coser L. (1970).The function of social conflict; the free press; New York.

Daniel Mekonen. (2016). Maaga indigenous conflict resolution institution among Libido Mareko Ethnic Group in Gurage Zone Southern Ethiopia.*International Journal of Scientific and Research Publications, 6.*

Deutsch, M. & Coleman, P. (2000). The handbook of conflict resolution: Theory and practice.San Francisco: Jossey-Bass.

Imobighe, T. (2003).The OAU(AU)and OAS in Regional conflict management a complete assessment,spectrum book limited.

Katz, D. (1965). Nationalism and strategies of international conflict resolution. In H.C. Kelman (ed.), International behavior: A social psychological analysis. pp. 356-390. New York: Holt, Rinehart & Winston.

Lambert M. & Myers, S. (1999). Activities for conflict resolution. Human Resourse Devlopment Press, US and Canada.

Leslu,W. (1973). English-Amharic context dictionary.Belgium, Sowtiz.

Melese, T.(2008). Gender role in *conflict*in Soddo Zuria Woreda of Wolaita Zone, Southern. Anthropology and Graduate Research in Ethiopia: Changes and Continuities at Addis Ababa University.

Netsanet D. (2006). The conflict management process through strategies encompasses in Southern WolloB.A Thesis, Addis Ababa University.

Robbins, P. Stephen & Seema,S. (2006), Conflict and negotiation from Organizational Behaviour., Singapore: Pearson education.

Rugugnamu, S. (2000). Conflict management in Africa diagnosis of current practice and prospects".(paper presented at the DPMF/OSSREA conference on African conflict reconstruction). Addis Ababa, Ethiopia.

Schmid,A. (2000).The function of social conflict. New York free press.

Tuan, H. (2006).*Decentralization and local politics of forest management in Vietnam: A Case Study of Co Tu Ethnic Community*.*Journal of Legal Pluralism*, 52.

Yohannes G.Michael, Kassaye Hadgu & Zerihun Ambaye. (2005). Addressing Pastoralists conlict in Ethiopia፡ The case of Kuraz and Hamer sub districts of south omo zone.

Zertman, W& Francis M. (1999). Conflict resolution in Africa. Washington DC, the brooking institution.

ብሩክ ያሬድ(2006)፡ ፡ ባህላዊ የግጭትአፈታት ዘዴ በኩስሜብሐረሰብ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ስነ ፁሁፍና ፎክሎር ትምርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ፡ ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተማ፡ ፡

ኤልያ ስወላንሰ (2006)፡ ፡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሃላባ ብሔረሰብበ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ስነ ፁሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ፡ ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተማ፡ ፡